በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

የመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ፣ ቁጥጥር እና ክትትልን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት /FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

መስከረም 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ) 1

ክፍል አንድ 4

መግቢያ 4

የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት ዓላማ 5

የክትትል ኦዲቱ አላማ 6

የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 6

የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Standards of follow up Audit) 7

ክፍል ሁለት 8

ግኝቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች 8

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥናት ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ .. 8

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 9

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በእቅድ የተያዘው የነዳጅ በጀት ከአፈፃፀሙ ጋር መጣጣሙን በተመለከተ፤ 11

በፌዴራል መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት መጠቀምን በተመለከተ፤ 13

ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ የሚወሰን መሆኑን በተመለከተ፤ ... 15

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታን በተመለከተ፤ 17

የተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎችን በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚጓዙትን ኪሎ ሜትር መጠን በተመለከተ፤ 22

ጌጃቸው (የኪሎ ሜትር ቆጣሪ) ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን በተመለከተ፤ 31

ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት መዘጋጀቱን እና መቅረቡን በተመለከተ፤ 33

የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ 37

የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ወጥ /standardized / እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ መኖሩን፣ ስለነዳጅ አጠቃቀም ስልጠና መሰጠቱን እና ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዘጋጀታቸውንና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፤ 41

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን፣ ስለተሽከርካሪዎች ብዛት፣ ዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት እና ኦዲትን በተመለከተ፤ 46

ክፍል ሦስት 48

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) 48

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 48

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው 49

ክፍል አራት 51

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 51

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

(Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2004/2005 ዓ.ም በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች፣ እንዲሁም ኤጀንሲው የተሰጡትን ማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር መግኤ/ፈ-7/1/871 ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው :-

- የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት አለማካሄዳቸውን፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት የሌላቸው መሆኑን፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደበው በጀት በዓመቱ የታቀደውን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ በጥናት ላይ አለመመስረቱን፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ

አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ አለመጠቀማቸውን፣

- ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ አለመሆኑን፣
- ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ መሠረት ያደረገ አለመሆኑን፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ አለመኖሩን እና በሥራ ላይ አለመዋሉን፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የማይታወቅ እና ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑን፣
- የፌደራል መንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የኪ/ሜትር ቆጣሪ /ጌጅ/ የማይሰራ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ያልተዘረጋ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣
- እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት በነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ በወቅቱ እርምጃ አለመወሰዱን፣

- የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለሁሉም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ተሸከርካሪዎች በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ አለማዘጋጀታቸው፣

- የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና አለመሰጠቱን፣ የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር አለመደረጉን፣

- የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሸርካሪዎች በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ አለመደረጉን፣

- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት እና የክትትልና ግምገማ ሥራ አለመከናወኑን፣

- በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሸከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ አለመያዛቸው፣

- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት አለመከናወኑን፣

እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የአገሪቱን ኢኮኖሚ ግንባታ በማቀላጠፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውን የትራንስፖርት አገልግሎት በይበልጥ ለማሻሻል ተሽከርካሪ የሚጠቀመው ነዳጅ ከአገሪቱ አቅምና ፍላጎት ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም ነዳጅ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን እና አስፈላጊ የሆኑ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

2. የኢትዮጵያ መንግስት ወደ አገር ውስጥ ከሚያስገባቸው የተለያዩ ምርቶች ውስጥ ነዳጅ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዝ እና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያወጣ መሆኑን መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2009/10 ወይም በ2002 በጀት ዓመት በጠቅላላው ብር 16,826 ሚሊዮን የሚያወጣ 1,994.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶንስ ነዳጅ (ፔትሮሊዬም) በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት አማካኝነት ወደ አገር ውስጥ ገብቷል፡፡ በአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ መናር ምክንያት ከ2008/9 ወይም 2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ31.6 በመቶ ጭማሪ የሚያሳይ መሆኑን የብሄራዊ ባንክ አመታዊ ሪፖርት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በ2003 በጀት ዓመት የነዳጅ ምርትን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት 1.7 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንደተደረገ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

3. ለፌዴራል መንግስት በ2002 ዓ.ም ከተመደበው አጠቃላይ በጀት ውስጥ ከስድሳ እስከ ሰባ በመቶ (ከ60% እስከ 70%) ያህሉ ለተለያዩ ንብረቶች እና አገልግሎቶች ግዥ ወጪ እንደሚውል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመንግስታዊ ሥራዎች ለማስፈጸም የትራንስፖርት አገልግሎት ለማከናወን ለነዳጅ ግዥ የሚውለው ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም በ2002 በጀት ዓመት ብር 444,632,802.74፣ በ2003 በጀት ዓመት ብር 651,765,752.71 ያህል ወጪ እንደተደረገ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አገሪቱ ያላትን

ውስን ሃብት ከፍተኛው ከውጭ አገር በሚገባ ምርት ላይ የምታውል በመሆኑ እና ይህንንም በቁጠባ፣ በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

4. የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 የተቋቋመ ሲሆን ኤጀንሲው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የግዥና ንብረት አስተዳደር ክንውንን ክትትል የማድረግ እና ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለመንግስት ጉዳይ ማስፈጸሚያ ለትራንስፖርት አገልግሎት ማከናወኛ ለሚውል በመንግስት የተመደበላቸውን የነዳጅ በጀት በወጣለት እቅድ መሠረት በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እያከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ይህን ከመንግስት በጀት ትልቅ ድርሻ ያለውን እና ለመንግስት ሥራ ማከናወኛ ወሳኝ ግብዓት የሆነውን ነዳጅ እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ኢኮኖሚያዊ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋለት መሆኑን፣ የመንግስት የግዥ መመሪያን ተከትሎ ግዥ ማከናወኑን፣ በመንግስት የተሽከርካሪ ሥምሪት አጠቃቀም እና ጥገና መሠረት የተገለጹ አሰራሮችን ጠብቆ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት ዓላማ

5. የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ዋና አላማ ለመንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የሚመደበውን የነዳጅ በጀት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ እንዲዘጋጅ በመርዳት ሀገሪቷ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ በመቀነስ እኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም ይህ ከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሚፈስበት ሀብት በአግባቡ ለታቀደለትና ለታለመለት አላማ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ አላማ

10. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2004/2005 ዓ.ም በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች፤ እንዲሁም ኤጀንሲው የተሰጡትን ማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር መግኤ/ፌ-7/1/871 ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

11. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006-2008 ዓ.ም ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እና ኤጀንሲው እነዚህን የኦዲት ግኝቶች የሚፈታበት የዖዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበትን የማሻሻያ እርምጃ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኤጀንሲው የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

12. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት ሲሆን ፣ በናሙና በተመረጡ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ለባህር ዳር ስታትስቲክ ቅ/ፅ/ቤት፣ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ(ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ለባህር ዳር

ዩኒቨርሲቲ (ፖሊ)፣ለማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ለጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር፣ለግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ለማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር መ/ቤቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Standards of follow up Audit)

13. የክትትል ኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች ቀደም ሲል በ 2004/2005 ዓ.ም በመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ በተከናወነው የክዋኔ ኦዲት በተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶችን ለማስተካከል የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች (Audit recommendation) መሰረት በማድረግ ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር የመጡ ለውጦችን ማየት እና ችግሮች ያልተሻሻሉ (ያልተቀረፉ) ከሆኑ ምክንያቶቹን በመመርመር የክዋኔ ኦዲቱ ያስገኘውን ውጤት መፈተሽ ነው፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥናት ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

14. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

15. በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ 9ኙ (በግዥና ንብረት አስተዳደር፣ በግብርና ሚ/ር፣ በማእድን ሚኒስቴር፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የበላይ ኃላፊዎች ነዳጅን በአግባቡ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እንዲካሄድ እና ሥልጠና እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ አለማከናወኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

16. የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ቢያከናውኑ ነዳጅን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንደሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

17. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ከተጠቃሚ መ/ቤቶች አስተያየቶች እንደቀረበ ገምግሞ እንደአስፈላጊነቱ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

18. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

19. በክትትል አዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ መ/ቤቶች መካከል በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ፖሊ ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ የማያውቅ ሲሆን፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት በሒደት ላይ ያለና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ስለተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት መጠናቱን ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

20. የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ2006 ዓ.ም ባከናወነው ኦዲት በቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በተገቢው መንገድ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርገቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

21. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

22. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የወጣ የተሽከርካሪ ጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ እንዳልነበረ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ10ሩ መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች ጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግል ማህደራቸው ከታዩት ተሽከርካሪዎች ከ2002 ዓ.ም. በፊት የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን የሚያመለክት እና የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃዎች የነበሩ ቢሆንም፣ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ግን መረጃዎችን ማግኘት አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

23. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት ቢኖራቸው ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ እንደሚረዳ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

24. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የተሽከርካሪ ጥገና መመሪያ የማዘጋጀት ባለሞያ አማካሪ ለመቅጠር (የአገልግሎት ግዢ ለመፈፀም) TOR ተዘጋጅቶ ጨረታ የወጣ መሆኑን እና በ 2005 ዓ.ምና በ2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

25. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

26. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን በተመለከተ በመረጃ ተይዞ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም ተሽከርካሪዎች በየ 5000 ኪ.ሜ ዘይት እንደሚቀየርላቸው፣ በየ10,000 ኪ.ሜ የዘይትና የናፍጣ ፊልትሮ እንደሚቀየርላቸው፣ በየ 25,000 ኪ.ሜ የእግር ሰርቪስ፣ ዲፈረንሻልና የካንቢዮ ዘይት እንደሚቀየርላቸው ፣ የመሪ እና የፍሬን ዘይት ሲያጎድሉ እንደሚሞላላቸው፣ በየወሩ ደግሞ ለትናንሽ ተሽከርካሪዎች 1 ኪሎ ፣ ለትላልቅ ተሽከርካሪዎች 2 ኪሎ ግሪስ እንዲጠጡ እንደሚደረግ፣

27. በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን በተመለከተ በየ10,000 ኪ.ሜ ልዩነት ሰርቪስ እንደሚደረጉ የስራ ጫና ሲበዛ ከዚህም ሊያልፍ እንደሚችል፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ለተሽከርካሪዎች ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን በተመለከተ በየ 5000 ኪ.ሜ ዘይት እንደሚቀየርላቸው፣ በየ10000 ኪ.ሜ ሰርቪስ እንደሚገቡ፣ ቢሆንም የተሽከርካሪ እጥረት ስላለ ተሽከርካሪዎች ያለ እረፍት ቀኑን ሙሉ የሚሰሩበት ሁኔታ መኖሩን፤

28. በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን በተመለከተ ተሽከርካሪዎች በመስክ ላይ እያሉ በየ 5,000 ኪ.ሜ ጥገና

እንደሚደረግላቸው፣ በየ10,000 ኪ.ሜ ደግሞ ሰርቪስ እንደሚደረግላቸው፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን በተመለከተ ሚ/ር መ/ቤቱ እራሱን የቻለ የተሽከርካሪዎች የጥገና ክፍልና ጋራዥ ያለው መሆኑን፣ተሽከርካሪዎችም በየ 5,000 ኪ.ሜ ዘይት እንደሚቀየርላቸው፣ በየ10,000 ኪ.ሜ ደግሞ ሰርቪስ እንደሚደረግላቸው፣ ተሽከርካሪዎች መስክ ላይ ሆነው ብልሽት ቢገጥማቸው በአካባቢው ባለው ሞኤንኮ አለዚያም የራሳቸውን መካኒኮች በመላክ ጥገና እንደሚደረግላቸው ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

29. በቤተመንግስት አስተዳደር የቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገላቸውና ቦሎ የሌላቸው ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት የተሽከርካሪዎች የጥገና ድግግሞሽ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፣ በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት የጥገና ድግግሞሽ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገላቸው 12 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኦዲት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ የቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገባቸውና ቦሎ የሌላቸውን ብዛት ያላቸው የተለያዩ መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በደብዳቤ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በእቅድ የተያዘው የነዳጅ በጀት ከአፈፃፀሙ ጋር መጣጣሙን በተመለከተ፤

31. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

32. ከ2002 እስከ 2003 ዓ.ም ባለው የበጀት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ 10 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በአራቱ (በ4) የነዳጅ በጀት (በሂሳብ መደብ 6217) ከአፈጻጸሙ ጋር ሲታይ የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሶስቱ ከ15% በላይ በጀቱን ሳይጠቀሙና አንድ መ/ቤት ደግሞ ከበጀት በላይ ወጪ አድርገው ተገኝተዋል፡፡ እነርሱም በማእድን ሚ/ር በ2002 ዓ.ም. (18.25%) እና 2003 ዓ.ም. (24.45%) ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2002 ዓ. ም (15.12%)

እንዲሁም በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት በ2003 ዓ.ም. (38.69%) ከተያዘላቸው በጀት በታች ተጠቅመው መገኘታቸው፡፡ እንዲሁም በጤና ጥበቃ ሚ/ር በ2002 ዓ.ም. የመንግስት የበጀት አዋጅ መመሪያ ሳይከተል ብር 62,350.8 (7.68%) ከተያዘለት በጀት በላይ መጠቀሙ ተገኝቶ ነበር፡፡

33. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደበው በጀት በዓመቱ የታቀደውን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ በጥናት ላይ መመሥረት እና አፈጻጸሙም በጀቱን በእቅዱ መሠረት በሚገባ መጠቀማቸውን የሚያመለክት ሊሆን እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

34. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ስለ በጀት አጠቃቀም ምላሽ አልሰጠም፡፡

35. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

36. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀትን በተመለከተ በጀት የሚያዘው ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ሳይሆን በጥቅል ለነዳጅ፣ለቅባት እና ለጥገና ተብሎ እንደሆነ፣ በጀቱም የሚያዘው ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም መሰረት በማድረግ እና አማካዩን በመውሰድ መሆኑን፣በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀትን በተመለከተ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ዋናው መ/ቤት እንደሚያዝላቸው፣

37. በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሚያዝ በጀት የሌለ መሆኑን፣ ነግር ግን ለነዳጅ፣ ለቅባትና ለጥገና ተብሎ ለሁሉም ተሽከርካሪዎች የሚያዝ መሆኑን፣ በጀቱም የሚያዘው ካለፈው ዓመት የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም በመነሳት አማካዩን በመውሰድ መሆኑን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀትን በተመለከተ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ሳይሆን በጥቅል ለነዳጅ፣ለቅባት እና ለጥገና ተብሎ ለትራንስፖርት ስምሪት ክፍል የሚመደብ መሆኑን አፈፃፀሙም

በፋይናንስ ክፍል እንደሚገኝ፣ በጀት የሚያዘው በተሽከርካሪዎች ቁጥር መሆኑን፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የበጀት እጥረት እንደሚገጥማቸው፤

38. በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀት የሚያዘው እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ከሚወስደው ነዳጅ ነባራዊ ሁኔታ እና ካለፈው አመት አፈፃፀም በመነሳት መሆኑን ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀትን በተመለከተ ከመንግስት የሚመደብ መደበኛ በጀት ያላቸው መሆኑን፣ ነገር ግን ከመንግስት የሚመደብላቸው በጀት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ የሩብ ዓመት ወጪያቸውን ስለማይሸፍን ከተራድዖ በሚገኝ ገንዘብ የዓመቱን ወጪ እንደሚሸፍን፣ በጀት የሚያዘውም በጥናት መሆኑን፤

39. በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደብ በጀትን በተመለከተ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለነዳጅ፣ዘይትና ቅባት ተብሎ የሚያዝ መሆኑን፣ በጀት የሚያዘው በጥናት መሆኑን ነግር ግን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የሚፈቀድላቸው በጀት ትንሽ መሆኑን ፣ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

በፌዴራል መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት መጠቀምን በተመለከተ፤

40. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

41. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከ11 መ/ቤቶች በ8ቱ በጋራ አገልግሎት ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሰራተኞችን በጋራ ተቀናጅተው ለሥራ የተሠማሩ እና የተጓጓዙ ስለመሆኑ ማስረጃ ተጠይቀው ሊያቀርቡ እንዳልቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

42. በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ መጠቀም ነዳጅን ለመቆጠብ እንደሚረዳ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

43. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፊ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ስለበጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ምላሽ አልሰጠም፡፡

44. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

45. በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) እና በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በጋራ በማቀናጀት እንደሚጠቀሙ ቢገልጹም ፣በጋራ ስለመጠቀማቸው የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑን እንዲሁም ተሽከርካሪ የሚጠየቀው በተዘጋጀ ፎርም ሳይሆን በቃል መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

46. በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን በጋራ በማቀናጀት እንደሚጠቀሙ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የስራ ጫና ያለባቸውን የስራ ክፍሎች ለክፍሉ የጋራ አገልግሎት ተሽከርካሪ የሚመደብላቸው ሲሆን ቁጥጥሩም በስራ ክፍሉ የሚደረግ መሆኑን፣ ሌሎች የስራ ጫና የሌለባቸው በጋራ በማቀናጀት እንደሚጠቀሙ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በአካባቢና ደን ጥበቃ ሚ/ር ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከተማ ሥራ፣ ለሰርቪስ ስራ አገልግሎትና ለሌላ ተብለው በየደረጃው ተሽከርካሪ የመመደብ ሥርዓት አለመኖሩን፣ በአዲግራት ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ ምደባ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን በጋራ በማቀናጀት (Pool) የማይጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በደብዳቤ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ የሚወሰን መሆኑን በተመለከተ፤

49. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

50. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ነዳጅን ለመቆጣጠር የሚያስችል በሳምንትም ሆነ በወር ለአንድ ተሽከርካሪ የተመደበ የነዳጅ መጠን የሚገልጽ ሰነድ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

51. በግብርና ሚ/ር የነዳጅ ኮታ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም፣ በወር የተወሰነው ኮታ ከ120-160 መሆኑ የግብርና ሚ/ር ከተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ሰሌዳ ቁ.4-14079 በ26 ቀን ውስጥ 510 ሊትር እና 4-00617 በ14 ቀናት ውስጥ 150 ሊትር ነዳጅ መቅዳታቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

52. ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ መወሰኑ ተገቢ ያልሆነ የነዳጅ ብክነትን ለመቅረፍ እንደሚያስችልየማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

53. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የውስጥ አሰራር እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን በማረጋገጥ በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

54. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

55. ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ እንደተገለፀው በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣ ለተሽከርካሪዎች የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. እንዲሁም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የነዳጅ እደላን በተመለከተ ለዳይሬክተሮች በየወሩ 120 ሊትር እንደሚቀዳላቸው፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፑል

ተሽከርካሪዎች ኮታ የሌላቸው መሆኑን፣ የዳይሬክተሮች ተሽከርካሪዎች ሁሉም ቤንዚን ሲሆኑ በወር 100 ሊትር ኮታ ያላቸው መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፡፡

57. በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር የፑል ተሽከርካሪዎች ስራ ስለሚበዛባቸው ኮታ የሌላቸው ሲሆን በኮታ የነዳጅ እደላ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ነገር ግን የተሽከርካሪ እጥረት ስላለባቸው በኮታው መሰረት እንደማይሄዱ፣ ተሽከርካሪዎች በሳምንት እስከ 120 ሊትር እንደሚቀዳላቸው፣ ለስራ ሃላፊዎች በወር 160 ሊትር ናፍጣ የሚቀዳላቸው መሆኑን ታውቋል፡፡

58. በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የፑል ተሽከርካሪዎች ኮታ የሌላቸው ሲሆን ለመ/ቤቱ ሃላፊዎች በሳምንት ቤንዚን ከሆነ 30 ሊትር ናፍጣ ከሆነ ደግሞ ከ 40-50 ሊትር እንደሚሰጣቸው፣ የሠራተኛ ሰርቪስን በተመለከተ የመንግስት ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት እያለ ኢኒስቲትዩቱ ለሰርቪስ ተሽከርካሪዎች በሳምንት የሰሌዳ ቁጥር 4-19379 አርባ ሊትር፣4-17189 ሁለት መቶ ሊትር፣ 4-03072 አንድ መቶ ሰማንያ ሰድስት ሊትር፣ 4-2757 አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሊትር እንደሚቀዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. በማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር የፑል ተሽከርካሪዎች ለናፍጣ በወር 220 ሊትር፣ ለቤንዚን /አውቶሞቢል/ 106 ሊትር የነዳጅ ኮታ ያላቸው ሲሆን ተሽከርካሪዎች የተመደበላቸውን ኮታ ሲጨርሱ በደብዳቤ ጠይቀው ተጨማሪ ሊትር የሚፈቀድላቸው መሆኑን፣እንዲሁም የመንግስት ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ለሁሉም የመንግስት ሰራተኞች የሰራተኛ ሰርቪስ አቅርቦ እያለ ሚ/ር መ/ቤቱ ለሰራተኛ ሰርቪስ ተሽከርካሪዎች በሳምንት 45 ሊትር እንደሚቀዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የነዳጅ እደላን በተመለከተ የፑል ተሽከርካሪዎች በሳምንት 40 ሊትር ሲቀዳላቸው የመንግስት ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት እያለ ለሰራተኛ ሰርቪስ ደግሞ እንደየእርቀታቸው ኮታ ያላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. በወሎ ዩኒቨርስቲ ለኃለፊዎች የተመደበ የነዳጅ ኮታ አለመኖሩን የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኦዲት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታን በተመለከተ፤

62. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

63. ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በወር የተመደበ የነዳጅ መጠን ናፍጣ እስከ 165 ሊትር እና ቤንዚን 135 ሊትር እንደሆነ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በ17/3/1997 በቁጥር ጠ80. አጠ3/101/02 በተጻፈው የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ ያመለክታል፡፡

64. ይሁን እንጂ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በግንቦት ወር 2004 ዓ.ም. ለሰሌዳ ቁጥር 4-14152 ለፕሬዝዳንቱ ተሽከርካሪ 450 ሊትር ነዳጅ እንዲሁም ለሰሌዳ ቁጥር 4-13617 ለምክትል ፕሬዝዳንቱ ተሽከርካሪ 300 ሊትር ነዳጅ ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ የተፈቀዳላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በሥራ ላይ ከዋለ ከነዳጅ፣ ቅባት እና ዘይት መመዝገቢያ ቅጽ ለማረጋገጥ መቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

65. ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ መሠረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባየማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

66. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፊ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የንብረት ኦዲት አስተዳደር ኦዲት ሲደረግ ማረጋገጥ እንደሚቻል እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

67. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

68. ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በወር የተመደበ የነዳጅ መጠን ናፍጣ እስከ 165 ሊትር እና ቤንዚን 135 ሊትር እንደሆነ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ

እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በ17/3/1997 በቁጥር ጠ80. አጠ3/101/02 በተጻፈው የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ ያመለክታል፡፡

69. ይሁን እንጂ በናሙና ከታዩ መ/ቤቶች መካከል በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር 4-20275፣4-20253፣ 4-15937 እና 4-14152 በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ የሌላቸው ሲሆን፣ ነዳጅ በጨረሱ ቁጥር እንደሚሞላላቸው፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር 4-10718 በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ የሌለው መሆኑን እንዲሁም ሌሎች የሃላፊ ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ እንደሌላቸው ፣በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ የሌላቸው ሲሆን ነዳጅ በጨረሱ ጊዜ እንደሚሞላላቸው፤

70. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ የሌላቸው መሆኑን፣በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት የበላይ ኃላፊዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለዋና ዳይሬክተር በሳምንት 50 ሊትር፣ ለምክትል ዋና ዳይሬክተር በሳምንት 60 ሊትር የሚቀዳላቸው መሆኑን፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎችን የነዳጅ ፍጆታ በተመለከተ ለዋና እና ለምክትል ስራ አስኪያጆች በየወሩ ናፍጣ ከሆነ 165 ሊትር፣ ቤንዚን ከሆነ ደግሞ 135 ሊትር እንደሚቀዳላቸው ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

71. በሰመራ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ አጠቃቀም በወር ለእያንዳንዱ ኃላፊ የተመደበ መጠን /ኮታ/ አለመኖሩን እንዲሁም በአካባቢና ደን ጥበቃ ሚኒስቴር የነዳጅ አጠቃቀም በወር ለእያንዳንዱ ኃላፊ በተመደበለት የነዳጅ መጠን /በኮታ/ እየተሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. እንዲሁም ከተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት እንደተቻለው የማዕድን ፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር የበላይ ሃላፊዎች የሠሌዳ ቁጥር ቁ 4-15852 ፣ የሆነ ተሽከርካሪ የጥቅምት ፣ የሕዳር ፣ የጥር ፣ የየካቲት ፣ የሚያዚያ እና የግንቦት ወር 2008 ዓ.ም ፍጆታው እንደየቅደም

ተከተላቸው በመብለጥ 21 ፣ 90 ፣ 90 ፣ 60 ፣ 95 ፣ እና 55 ሊትር ናፍጣ ከኮታ በላይ የተጠቀሙ ሲሆን በጠቅላላው ከጥቅምት እስከ ግንቦት/2008 ዓ.ም 411 ሊትር ናፍጣ ከኮታ በላይ የተጠቀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

73. በጤና ጥበቃ ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-15034 የሆነ የበላይ ሃላፊ ተሽከርካሪ በወር የተተመነለት ኮታ 165 ሊትር ሲሆን፣ በመስከረም 2006 ዓ.ም 583.99 ሊትር፣ በጥቅምት 2006 ዓ.ም 590 ሊትር፣ በህዳር 2006 ዓ.ም 339 ሊትር፣ በሚያዚያ 2006 ዓ.ም 440 ሊትር ፣ በሰኔ 2006 ዓ.ም 526.45 ሊትር፤ በሀምሌ 2006 ዓ.ም 490 ሊትር ሲሆን፣ በ2007 ዓ.ም ደግሞ በመስከረም 2007 ዓ.ም 441.06 ሊትር፣ በየካቲት 2007 ዓ.ም 589.52 ሊትር፣ በሚያዚያ 2007 ዓ.ም 440 ሊትር፤ በሀምሌ 2007 ዓ.ም 589.91 ሊትር፤በነሀሴ 2007 ዓ.ም 570.62 ሊትር እንዲሁም በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም 575 ሊትር፣ በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም 550.87፣ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም 690 ሊትር፣ በታህሳስ 2008 ዓ.ም 528 ሊትር፤በሚያዚያ 2008 ዓ.ም 590 ሊትር፣ በግንቦት 2008 ዓ.ም 694 ሊትር ናፍጣ የተቀዳለት መሆኑ፣

74. በጤና ጥበቃ ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-15033 የሆነ የበላይ ሃላፊ ተሽከርካሪ ደግሞ በወር የተተመነለት ኮታ 165 ሊትር ሆኖ ሳለ በመስከረም 2006 ዓ.ም 336.9 ሊትር፤ በጥቅምት 2006 ዓ.ም 338.21 ሊትር፤ በህዳር 2006 ዓ.ም 330.78 ሊትር፣ በሚያዚያ 2006 ዓ.ም 470.75 ሊትር፤ በሰኔ 2006 ዓ.ም 474 ሊትር፤በሀምሌ 2006 ዓ.ም 460.03 ሊትር ሲሆን ፣ በ2007 ዓ.ም ደግሞ በመሰውከረም 2007 ዓ.ም 512.22 ሊትር፤ በየካቲት 2007 ዓ.ም 252 ሊትር፤በሚያዚያ 2007 ዓ.ም 470.75 ሊትር፤በሀምሌ 2007 ዓ.ም 410 ሊትር፤በነሀሴ 2007 ዓ.ም 410 ሊትር እንዲሁም በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም 696 ሊትር ፤በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም 470 ሊትር፣ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም 734.22 ሊትር፣ በታህሳስ 2008 ዓ.ም 521 ሊትር፣ በሚያዚያ 2008 ዓ.ም 590 ሊትር፣ በግንቦት 2008 ዓ.ም 685 ሊትር ናፍጣ የተቀዳለት መሆኑን፣

75. በጤና ጥበቃ ሚ/ር በተጨማሪም የሰሌዳ ቁጥሩ 4-18661 የሆነ የበላይ ሃላፊ ተሽከርካሪ በወር የተተመነለት ኮታ 165 ሊትር ሲሆን በየካቲት 2007 ዓ.ም 585.09

ሊትር፤ በነሀሴ 2007 ዓ.ም 563 ሊትር፤ እንዲሁም በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም 429.52 ሊትር ፤ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም 425 ሊትር፤ በጥር 2008 ዓ.ም 460 ሊትር፤ ናፍጣ የተቀዳለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ስለመኖሩ በተመለከተ፤

76. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

77. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በሁሉም የተለያዩ ቅጾች ፎርማት ቢያዘጋጁም ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ነዳጅ ሲቀዳ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ተሽከርካሪው ሲሰማራ የሄደበት እና የሚመለስበት ሰዓት በተዘጋጁት ቅጾች ላይ የማይመዘገብ መሆኑን ሥራ ላይ ከዋሉ የነዳጅ መመዝገቢያ ቅጾች ላይ ለማረጋገጥ መቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

78. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ቢኖር እና በሥራ ላይ ሊውል እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

79. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፌ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የተላኩትን ቅፆች ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ በ2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

80. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

81. ከመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ሪፖርት ለመመልከት እንደተቻለው በፍትህ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች 04፣05፣09፣12 እና 13 ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ አባሪ ላይ ያሉትን ቅፆች ማለትም ቅፅ 01፣02፣05፣እና 12 ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ አባሪ ላይ ያሉትን ቅፆች ማለትም ቅፅ 02፣07፣እና 08 ስራ ላይ አለመዋላቸው፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ቅፅ 02፣05፣07፣እና 12 ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣ በቤተመንግስት አስተዳደር የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ቅፅ 05 እና 07 ጥቅም ላይ አለመዋላቸው ፣

82. በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ቅፅ 1፣2፣3፣4፣5፣8፣9፣10፣11፣12፣13 ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን መዝግቦ አለመያዙ ፣ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን መዝግቦ አለመያዙን፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ አባሪ ላይ ያሉትን ቅፆች ማለትም ቅፅ 01፣02፣05፣እና 12 ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑን፤

83. በመንግስት የልማት ድርጅት ባላደራ ቦርድ የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን መዝግቦ አለመያዙን፣ በቤተመንግስት አስተዳደር የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ቅፅ 05 እና 07 ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ የተሽከርካሪዎችን የነዳጅና የቅባት በኪሎ ሜትር የፈጀውን ለመቆጣጠርና ለክትትል የሚያገለግለውን መመሪያ ቁጥር 32/2004 ቅጽ 02 እና 03 አገልግሎት ላይ አለመዋሉ እና ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ሪፖርቱ እንዲላክ አለመደረጉን፣በሰመራ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ አጠቃቀም ከቅጽ 01 እስከ ቅጽ 013 ያሉት በመመሪያው መሠረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣-በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ

እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን መዝግቦ አለመያዙን ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት እንደቻለው በናሙና በታዩ መ/ቤቶች ማለትም በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ ኤፍ ቢ ፣ ዘንዘልማ ፣ ይባብ ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በማዕድን፣በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በስታትስቲክስ ባህርዳር ቅርንጫፍ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር እና በግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ የሌለ ሲሆን በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ምንም ዓይነት ቅፅ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

85. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ የተለያዩ ቅፆችን ስራ ላይ የማያውሉ መ/ቤቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በደብዳቤ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

የተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎችን በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚጓዙትን ኪሎ ሜትር መጠን በተመለከተ፤

86. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

87. በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 11 መ/ቤቶች በ7ቱ፣ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ ሰነድ አለማዘጋጀታቸው እና ተግባራዊ አለማድረጋቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

88. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር

መጓዝ እንደሚችል መታወቁና እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

89. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ኖርማላይዜሽን ተሰርቶ በየመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር እንደሚጓዙ መረጃ መያዛቸውን ክትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

90. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

91. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለመመልከት እንደተቻለው በናሙኑ የተወሰዱ መ/ቤቶች ያሉ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ ልኬት የማይደረግላቸው ሲሆን በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል ልኬት የተደረገው በ 2004 ዓ.ም መሆኑን አሁን ተሽከርካሪዎች ልኬት በምርታማነት ኤጀንሲ እየተደረገላቸው መሆኑን የቀድሞው ልኬት ማስረጃም ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑን፣ በማዕድን ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል በቃል ደረጃ የሚታወቅ ሲሆን በሰነድ ልኬት የተደረገበት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተሽከርካሪዎቹ ልኬት እየተደረገላቸው እንደሆነ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሀላፊዎች ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል ያልተለካ መሆኑን ከተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ስታንዳርድ/ኖርም/ ማስረጃ ታውቋል፡፡

93. እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት ለተሽከርካሪዎች ልኬት /ኖርማላይዜሽን/ አለመደረጉን፣በኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን ፣ በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚገኙ

ተሽከርካሪዎች በከፊል ብቻ ለተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን የተሰራ መሆኑን እና ለሁሉም ተሽከርካሪዎች በተሟላ ሁኔታ አለመሰራቱን፣ በሰመራ ዩኒቨርስቲ አንድ ተሽከርካሪ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር ሊጓዝ እንደሚችል የሚያሳይ /ኖርማላይዜሽን/ የሰነድ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑን፤

94. በብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በ2005 ዘመን በተዘጋጀ የተሽከርካሪዎች ነዳጅ ስርጭት መቆጣጠሪያ ኖርማላይዜሽን መሠረት እስካሁን የሚጠቀም መሆኑን እና በ2006 ዘመን የሚስተካከለው ተስተካክሎ በአዲስ ተከልሶና ታርሞ ያልተዘጋጀና ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ፣በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት የተሽከርካሪ ስምሪት ክፍሉ በቆየ እና ወቅታዊ ባልሆነ በ2005 ዘመን በተዘጋጀ ኖርማላይዜሽን መሰረት እየተጠቀመ መሆኑ እና በአዲስ ተከልሶ የተዘጋጀ ኖርማላይዜሽን አለመኖሩን፣ በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ለተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ኖርማላይዜሽን ያልተሰራላቸው እና በዚያ መሰረት ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን፤

95. በኢትዮጵያ ካይዘን ኢንሰቲትዩት የተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን ቢኖርም ወቅታዊ አድርጎ አለመጠቀሙን፣ በብሔራዊ ስነ ልክ ኢንስቲትዩት የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ለሚጠቀሙበት የነዳጅ ፍጆታ ለመቆጣጠር እንዲቻል ለሦስት መኪኖች ኖርማላይዜሽን እንዲሰራ አለመደረጉ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ለተሽከርካሪዎች በሊትር በአማካይ የሚሄዱበት ኪሎ ሜትር ኖርማላይዜሽን ያልተሰራላቸው መሆኑ፣ በአካባቢና ደን ጥበቃ ሚኒስቴር የነዳጅ አጠቃቀም ኖርማላይዜሽን አለመሠራቱን፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሽከርካሪ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚጓዝ የሚያረጋግጥ በጥናት ላይ የተመሠረተ ኖርማላይዜሽን ያልተሰራ መሆኑ፤

96. በአገር አቀፍ ትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ አንድ ተሽከርካሪ በሊትር መሄድ ያለበትን ኪሎ ሜትር /ኖርማላይዜሽን/ የሚያሳይ ጥናት አለመኖሩን፣ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ተሽከርካሪዎች በኪሎ ሜትር ምን ያህል እንደሚጓዙ የሚገልጽ /ኖርማላይዜሽን/ አለመዘጋጀቱ፣ በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ ብዛታቸው 2 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን /በአማካይ በሊትር የሚጓዘው ኪ.ሜትር ያልተሰራላቸው መሆኑን፣ በመቱ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርሲቲውን

ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል /ኖርማላይዜሽን / ተሽከርካሪቹ በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር እንደሚጓዙ የሚገልጽ በኮሚቴ ተጠንቶ ተግባር ላይ ያልዋለ መሆኑን፣ ከመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ሪፖርት ለማረገገጥ ተችሏል፡፡

97. በተጨማሪም ከተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት እንደተቻለው በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፡-

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-01792 የሆነ ተሽከርካሪ በሀምሌ 2006 ዓ.ም በአማካይ በሊትር 5.55 ኪ.ሜ መጓዝ ሲኖርበት በሊትር 4.3 ኪ.ሜ ተብሎ የተመዘገበ መሆኑን ፣ የተቀዳለት ሊትር 100 ሲሆን በዚሁም መሰረት በወር ውስጥ 555 ኪ.ሜ መጓዝ ሲኖርበት 430 ኪ.ሜ ተብሎ መገለፁን፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-01792 የሆነ ተሽከርካሪ በነሀሴ 2006 ዓ.ም በአማካይ በሊትር 5.55 ኪ.ሜ መጓዝ ሲኖርበት በሊትር 2.83 ኪ.ሜ ተብሎ የተመዘገበ መሆኑን፣ የተቀዳለት ሊትር 150 ሲሆን በዚሁም መሰረት በወር ውስጥ 832.5 ኪ.ሜ መጓዝ ሲኖርበት 425 ኪ.ሜ ተብሎ መገለፁን፤

98. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ደግሞ ፡-

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-07813 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 8 ኪ.ሜ. ሲሆን ተሽከርካሪው በኅዳር 2008 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 113 ሊትር ነው፡፡ በዚሁ በኅዳር ወር የተጓዘው ኪ.ሜ.800 መሆኑን ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /800/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር/113/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 8 ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 13 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10755 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 2.5 ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 1680 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ. 3205 መሆኑ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /3205/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር/1680 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር

እንዲጓዝ ከተተመነለት 2.5 ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 408 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ ፤

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10758 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 8.5 ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 540 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ .4307 መሆኑ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /4307/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር/540/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 8.5ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 33 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይመሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04600 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9 ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 206.01 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.1441 መሆኑ ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /1441/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /206.01/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9 ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 45 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-4596 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9 ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 315 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2295 መሆኑ ፣ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2295/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /315/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 60 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-02248 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9 ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 476.15 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.3266 መሆኑ ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /3266/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /476.15/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 113.3 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10235 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኀዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 293 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2143 መሆኑ ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2143/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /293 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ ወይም 54.8 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-13317 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኀዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 300 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.1620 መሆኑ ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /1620/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /300 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 120 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-1077 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 7ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 420 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ /1180/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /420/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 7ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 251.4 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-1225 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 80 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.360 መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /360/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /80 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 40 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04527 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኀዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 228 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.1525 መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪው

የተጓዘው ኪ.ሜ /1525/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /228/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9 ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 58.5 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤

- የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07633 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 341.17 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2410 መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2410/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /341.17 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 73.3 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-12412 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 354 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2721 መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2721/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /354 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 51.6 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 3-08985 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 307 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2272 መሆኑ ፣ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2272/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /307 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 54.5 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-02414 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 8.5ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 173 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.872መሆኑ ከተዘጋጀው ቅጽ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /872/ የተጠቀመው

ነዳጅ በሊትር /173/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 70.4 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤

- በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -13544 የሆነው ተሽከርካሪ 177 ሊትር፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10763 የሆነው ተሽከርካሪ 781.42 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -15105 የሆነው ተሽከርካሪ 106.7 ሊትር፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-03633 የሆነው ተሽከርካሪ 57 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4- 04206 የሆነው ተሽከርካሪ 34 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4-05633 የሆነው ተሽከርካሪ 47.7 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -13544 የሆነው ተሽከርካሪ 117 ሊትር ፣ብልጫ መጠቀማቸውን ከተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥሩ 4- 04206 የሆነው ተሽከርካሪ 34 ሊትር፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-05633 የሆነው ተሽከርካሪ 47.7 ሊትር፣
- በህዳር ወር 2007 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥሩ 4-14256 የሆነው ተሽከርካሪ 398.2 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4-08865 የሆነው ተሽከርካሪ 60 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 3-08273 የሆነው ተሽከርካሪ 842.6 ሊትር ብልጫ መጠቀማቸውን ከተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በመስከረም 2008 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥሩ 4-02414 የሆነው ተሽከርካሪ 70.5 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10673 የሆነው ተሽከርካሪ 394 ሊትር፣የሰሌዳ ቁጥሩ 4-10678 የሆነው ተሽከርካሪ 37 ሊትር ብልጫ መጠቀማቸውን ከተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት ተችሏል፡፡

99. ከተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት እንደተቻለው በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፡-

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-15386 የሆነው ተሽከርካሪ በጥር ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው 2025 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 225 ሊትር ሲሆን ለዚህ ርቀት የተቀዳው ነዳጅ 275 ሊትር መሆኑ ወይም 50 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን ፤

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -17016 የሆነ ተሽከርካሪ በየካቲት ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 5336 ኪ.ሜ ነው:; ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 476 ሊትር የነበረ ሲሆን የተቀዳው ነዳጅ 748 ሊትር መሆኑ ወይም 272 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -15470 የሆነ ተሽከርካሪ በየካቲት ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 3360 ኪ.ሜ ነው:; ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 480 ሊትር የነበረ ሲሆን የተቀዳው ነዳጅ 567 ሊትር መሆኑ ወይም 87 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -12976 የሆነ ተሽከርካሪ በሰኔ ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 1909 ኪ.ሜ ነው:; ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በኖርማላይዘሽኑ መሰረት 763 ሊትር የነበረ ሲሆን የተቀዳው ነዳጅ 830 ሊትር መሆኑ ወይም 67 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -14152 የሆነ ተሽከርካሪ በሰኔ ወር 2006 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው 31635 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 450 ሊትር የነበር ሲሆን የተቀዳው ነዳጅ 470 ሊትር መሆኑ ወይም 20 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -115057 የሆነው ተሽከርካሪ በሀምሌ ወር 2007 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 2093 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 837 ሊትር የነበረ ሲሆን ለዚህ ርቀት የቀዳው ነዳጅ 910 ሊትር መሆኑ ወይም 73 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -17092 የሆነው ተሽከርካሪ ጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 6332.5 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 744 ሊትር የነበረ ሲሆን ለዚህ ርቀት የተቀዳው ነዳጅ 1210 ሊትር መሆኑ ወይም 466 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -20494 የሆነ ተሽከርካሪ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 6721.2 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ

መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 840 ሊትር የነበር ሲሆን ለዚህ ርቀት የቀዳው ነዳጅ 914 ሊትር መሆኑ ወይም 74 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣

100. በጤና ጥበቃ ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-02822 የሆነው ተሽከርካሪ በጥር ወር 2008 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 240 ኪ.ሜ ነው:: ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በኖርማላይዘሽኑ መሰረት 40 ሊትር ነበር:: ነገሪግን ለዚህ ርቀት የቀዳው ነዳጅ 340 ሊትር መጠቀሙን ከተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ ለመመልከት ተችሏል፡፡

101. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ ሰነድ በተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ አመዘጋገብ መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

ጌጃቸው (የኪሎ ሜትር ቆጣሪ) ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

102. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

103. በናሙና ከተመረጡ 11 የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች በ10ሩ ጌጃቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ከማድረግ ወጪ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

104. የፌደራል መንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪ በኪሎ ሜትር የነዳጅ ፍጆታቸውን ለማወቅ እና ለመቆጣጠር የተሽከርካሪው ኪ/ሜትር ቆጣሪው /ጌጁ/ የሚሠራ መሆኑ ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደተጓዙ ለማወቅ እንደሚያስችልየማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

105. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ክትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

106. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

107. በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) የሰሌዳ ቁጥር 4-2416፣ 4-08817፣ 4-07854፣ 4-10673፣ 4-09584፣ 4-02437 እና 4-2428 ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ የሰሌዳ ቁጥር 4-09583 የሆነ ተሽከርካሪ ጌጁ የማይሰራ መሆኑን ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-05450፣ 4-03448፣ 4-05948፣ 4-13223፣ 4-17128፣ 4-08495 ተሽከርካሪዎች የማይሰራ መሆኑን፣የተሽከርካሪ እጥረት ስላለባቸው ጌጃቸወው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎችን እንደማያቆሟቸው፤

108. በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት የሰሌዳ ቁጥር 4-02757፣ 4-03072፣ 4-04163፣ 4-02199፣ 4-019158፣ 4-02777፣ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ አብዛኛው ተሽከርካሪ 15 እና 20 ዓመት የሰሩ በመሆናቸው መለዋወጫ ጌጅ ለማግኘት እንደማይቻል፣ ተሽከርካሪዎቹ እንዳይቆሙ የተሽከርካሪ እጥረት ያለባቸው እንደሆነ፣በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-00109 እና 4-05708 የሆኑ የጭነት ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ ሲሆን ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሁሉም ተሽከርካሪዎች ኪ/ሜትር ቆጣሪ /ጌጁ/ የሚሠራ መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

109. በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04416 የሆነ ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጁ የማይሰራ መሆኑን እንዲሁም በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል ያልተለካ መሆኑን ከተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ስታንዳርድ/ኖርም/ ማስረጃ ለማወቅ መቻሉ፤

110. ከመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ሪፖርት ለመመልከት እንደተቻለው በቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር መለኪያ /ጌጅ/ ሳይሰራ ለስራ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር 4-17387 ዳዎ አውቶቡስ፣ 4- 16543 ሰንሎግ አውቶቡስ፣ 4- 16041 ፒክአፕ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ፣ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ባለስልጣን በመ/ቤቱ ውስጥ በሰርቪስ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው ሳይሰራ ወደ ስራ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ኮድ ቁጥር 4-00008፣ ኮድ ቁጥር 4-000 መሆኑ፤

111. በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ጌጁ የማይሰራ ተሽከርካሪ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ የሰሌዳ ቁጥራቸው 4-04153 DAF /ዳፍ/ ፣ 4-05810 Mercedes የሆኑት የጭነት ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው ባለመሥራቱና በማርጀታቸው ምክንያት መጠነኛ ዕድሳት እየተደረገላቸው በመስክ ሥራ ላይ የቆዩ መሆኑ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብዛታቸው 4 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ በባህር ዳር ዩንቨርስቲ ጌጃቸው የማይሰራ የሰሌዳ ቁጥራቸው 4-02416፣ 4-02430፣ 4-08817፣ 4-10672 የሆኑ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን፣ በወሎ ዩኒቨርስቲ የሰሌዳ ቁጥር 4-14749፣ 4-12468 የሆኑ ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የሰሌዳ ቁጥር 4-12976 የሆነ ተሽከርከሪ ጌጁ የማይሰራ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የሰሌዳ ቁጥር 4-1162 የሆነ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ያለ አንድ ተሽከርካሪ ጌጁ የማይሰራ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

112. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ያላቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲስዱ በደብዳቤ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት መዘጋጀቱን እና መቅረቡን በተመለከተ፤

113. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

114. በናሙና ተመርጠው በኦዲት በታዩ 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በቅጽ ላይ በመሙላት በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

115. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ

የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

116. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፊ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ክትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

117. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

118. በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደማያሳውቁ፣ ለዋናው መ/ቤት በየ ሩብ ዓመቱ ብቻ እንደሚያሳውቁ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደማይቀርብ የሚቀርበው በጥቅል መሆኑን እንዲሁም በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲሁም ለግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

119. በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ 2006 ዓ.ም ሁሉም ተሽከርካሪዎች እለታዊ የነዳጅ፣የዘይትና የኪ.ሜ ያልተመዘገበ መሆኑን ከተሽከርካሪዎች የግለ ማህደር ለመመልከት መቻሉን፣

120. በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፡-

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-16187 የሆነ ተሽከርካሪ በሀምሌ 2006 ዓ.ም እለታዊ የነዳጅ መመዝገቢያ የሚያሳየው በወሩ ውስጥ የተጠቀመው የነዳጅ መጠን 150 ሊትር ሲሆን የወሩ ላይ ደግሞ 278 ሊትር ተብሎ የተገለፀ መሆኑን፣

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04411 የሆነ ተሽከርካሪ እለታዊ የነዳጅ መመዝገቢያ የሚያሳየው በወሩ ውስጥ የተጠቀመው የነዳጅ መጠን 40 ሊትር ሲሆን የወሩ ላይ ደግሞ 64.22 ሊትር ተብሎ የተገለፀ መሆኑን ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04411 የሆነ ተሽከርካሪ በጥር ወር በሊትር የተጓዘው 5.13 ኪሎ ሜትር ሲሆን በወሩ ውስጥ የተቀዳው 229 ሊትር ሆኖ ወርሀዊ ሪፖርት ላይ 160 ሊተር ተብሎ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04411 የሆነ ተሽከርካሪ በነሀሴ ወር 2006 ዓ.ም በሊትር የተጓዘው 5.6 ኪሎ ሜትር ሲሆን በወሩ ውስጥ የተቀዳው 202.5 ሊትር ሆኖ ወርሀዊ ሪፖርት ላይ 160 ሊተር ተብሎ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ፤
- በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-04411 የሆነ ተሽከርካሪ የሀምሌ ወር 2006 ዓ.ም እለታዊ የነዳጅ መመዝገቢያ የሚያሳየው በወሩ ውስጥ የተጠቀመው የነዳጅ መጠን 40 ሊትር ሲሆን የወሩ ላይ ደግሞ 64.72 ሊትር ተብሎ የተገለፀ መሆኑን፤

ከተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ለመመልከት መቻሉ፤

121. በተጨማሪም በኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ለተሽከርካሪዎች የሚወጡ ከፍተኛ ወጪዎች ንብረቱ በአግባቡ በቋሚ ንብረት መዝገብ ላይ ተደምሮ አለመተከሉን፣ የነዳጅ እና የቅባት ወጪ እየተመዘገበ በየሶስት ወሩ ለመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑን፤ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሚያዚያ ወር /2006 ዓ.ም በተዘጋጀው ወርሃዊ ሪፖርት የሰሌዳ ቁጥሩ 4-01918፣ 4-02756፣ 4-01902፣ 4- 02761፣ 4-02765፣ 4-16377፣ 4-02753፣ 4-02755፣ 4-02775፣ 4-01919፣ 4-02760 4-05577 ፣ 4-16229፣ 4-04413 4-11134፣ 4-11136፣ 4-02056፣ 4-022502፣ 4-02534፣ 4-02591፣ 4-04454፣ 4-04302፣ 4-08555፣ 4-09279፣ 4-04274፣ 4-8087፣ 4-01094፣ 4-02181፣ 4-02755፣ 4-02906፣ 4-02059፣ 4-02168 4-2753 የሆኑ ተሽከርካሪዎች በወሩ ውስጥ የተቀዳው ነዳጅ በሊትር ፣ የተነዳው ኪሎ ሜትር ፣ የወጣው ወጪ ተብሎ በተዘጋጀው ሰንጠረዥ ላይ ያልተሟላ መሆኑ፣

122. በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተሽከርካሪ ዘይትና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃዎችን ለሚመለከታቸውና ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ ተጠናቅሮ የማይላክ መሆኑን ፣ በሰመራ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ የስምሪት ሁኔታ ፣ የጥገና ወጪ፣ የመለዋወጫ ግዥ በየሩብ ዓመቱ ለዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑን ፣ በትምህርት ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች ስምሪት ሁኔታ፣ የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ግዢ ወዘተ. መረጃ በየሩብ ዓመቱ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይላክ መሆኑን፣

123. በኢትዮጵያ እንቨስትመንት ኮሚሽን የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀም መረጃዎች ለሚመለከታቸውና ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ እንደማይላክ ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ለዩኒቨርሲቲው ለበላይ ኃላፊ በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ ፣ በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን የተሽከርካሪ የስምሪት ሁኔታ፣ የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ግዢ ወዘተ. መረጃ በየሩብ ዓመቱ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይቀርብ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ኀረስ ድርጅት የጥገና አገልግሎት ፣ የመለዋወጫ ግዢ ወዘተ.መረጃዎች በየሩብ ዓመቱ አዘጋጅተው ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይቀርብ መሆኑን፣

124. በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል የተሽከርካሪ ጥገና ወጭ በየሩብ ዓመቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፣ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ ዘይትና ቅባት አጠቃቀም በየ3 ወሩ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት የማይላክ መሆኑ፣ በደብረታቦር ዩኒቨርስቲ የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ግዥ ወዘተ.መረጃዎች በየሩብ ዓመቱ አዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይቀርብ መሆኑ፣ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ተሽከርካሪዎች ነዳጅና ቅባት በኪሎ ሜትር የፈጁትን ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስፈልገውን መመሪያ ቁጥር 32/2004 ቅጽ 02 በአገልግሎት ላይ እንዲውል አለመደረጉና ሪፖርት ተዘጋጅቶ በየወሩ ለዩኒቨርስቲው የበላይ ኃላፊ እና ለመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር የማይላክ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

125. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ለሁሉም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት ወርሃዊ የተሽከርካሪ

ነዳጅ፣ ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ሪፖርት በየወሩ መጨረሻ ሪፖርት እንዲደረግ ሐምሌ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ማሳሰባቸውን ገልፀዋል፡፡

126. ይሁን እንጂ ክፍተቱ የክትትል ኦዲት እስከተጠናቀቀበት እስከ መስከረም 2009 ዓ.ም ድረስ መኖሩ ታውቋል፡፡

የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ

127. በከዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

128. በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ከኮታ በላይ ሲጠቀሙ በነበሩ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት በ1 ሊትር ከወጣላቸው የኪ.ሜ. ልኬት በታች ያሽከረከሩ አሽከርካሪዎችን በመለየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

129. እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት በነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

130. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ክትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

131. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

132. በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት የተሽከርካሪ ስምሪት ባለሞያ አለመኖሩን፣ የስምሪት ስራው እየተሰራ ያለው በፋይናንስና ግዢ የሥራ ዘርፍ ተደርቦ መሆኑን፣ ይህ ደግሞ በስራቸው ላይ ጫና እየፈጠረባቸው ሲሆን ችግሩም ለረጅም ጊዜ ያልተቀረፈ እንደሆነ እንዲሁም በቅ/ፅ/ቤቱ እራሱን የቻለ የጥገና ባለሞያ አለመኖሩን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ምንም ዓይነት ቅፅ የሌላቸው መሆኑን ነገር ግን አሁን ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣

133. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች ልኬት/ ኖርማላይዜሽን/ በየዓመቱ እንደማይደረግ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ለነዳጅ የሚመደበው በጀት

ዝቅተኛ መሆኑን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ነዳጅን በሚመለከት የሚመጡ መመሪያዎች ግልፅ አለመሆናቸውን፣ የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚልኩት የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ አለመሰጠቱን፣

134. በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር አብዛኛው ተሽከርካሪዎች ያረጁ መሆናቸውን፣ ወደ 34 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ሊወገዱ መሆናቸውን እንዲሁም ከዚህ ቀደም 456 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ ያደረጉ መሆኑን፣ የሹፌር እጥረት ያለባቸው ሲሆን የስምሪት አገልግሎት በሁለት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰራ፣ በማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር የስምሪት ሰራተኛ የሌለ መሆኑን፣ ስራው እየተሰራ ያለው በንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ኬዝ ቲም ኃላፊ እና በውሰት ከሌላ ክፍል በመጣ ሰራተኛ መሆኑን፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ነዳጅ የሚቀዱት ከ አ/አ ዩኒቨርሰቲ በዱቤ እንደሆነ፣ ነዳጅ የማይገኝበት ወቅት መኖሩን፣ብዙ መስሪያ ቤቶችም በወረፋ ስለሚቀዱ በነዳጅ ስርጭት ወቅት ወረፋ የሚበዛ መሆኑን ፣ የነዳጅ መቅጃው ያረጀ ስለሆነ ሶስትና አራት ቀን የማይሰራበት ጊዜ መኖሩን ይህም የሥራ ጫና የፈጠረባቸው እና ስራ የሚያስተጓጉል መሆኑን ከሚመለከተቻው የስራ ኃላፊዎች ተረድተናል፡፡

135. እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር የተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ ፣ ተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ ፣ዘይት፣ ቅባት ፍጆታ መጠን የጥገና ወጪ የተጓዘው ኪሎ ሜትር መጠን በእንማን ይዞታ ስር እንደነበረ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖሩ፣ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣ ተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ ፣ ዘይት፣ ቅባት ፍጆታ መጠን የጥገና ወጪ የተጓዘው ኪሎ ሜትር መጠን በእነማን ይዞታ ስር እንደነበረ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖሩ፤

136. በኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣ ተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ

በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት፣ ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣የተጓዘው ኪሎ ሜትር መጠን ፣ በእነማን ይዞታ ስር እንደነበሩ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖሩን ፣ በብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ጽ/ቤት የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣ የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት፣ እና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣የተጓዘው ኪሎ ሜትር መጠን ፣ በእነማን ይዞታ ስር እንደነበሩ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ የመረጃ ቋት አለመኖሩን፣

137. የመቱ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪን የሕይወት ታሪክ የሚያሳይ የግል ማህደር በተሟላ መልክ አለመያዙን ፣ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ በተሽከርካሪ የግል ማህደር ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ መረጃዎች ማለትም ተሽከርካሪው የተገዛበት ዓመተ ምህረት፣ የተገዛበት ዋጋ፣ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመው የነዳጅ መጠን፣ በእነማን ይዞታ ስር እንዳለ የሚያሳይ መረጃ ያልተካተተ መሆኑን ፣ በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በተሽከርካሪ የግል ማህደር ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ መረጃዎች ማለትም ተሽከርካሪው የተገዛበት ዓመተ ምህረት፣ የተገዛበት ዋጋ ያልተቀመጠ መሆኑ ፣

138. በብሔራዊ ስነ ልክ ኢንስቲትዩት የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ፣ የተሽከርካሪዎቹ የስምሪት ሪፖርት ፣ የነዳጅ እና የጥገና ወጪን በዝርዝር በትክክል ተመዝግቦ እንዲያዝ አለመደረጉን ፣በመንግስት ከሙኒኬሽን ጽ/ቤት የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፤ የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፤የተጉዋዘው የኪ/ሜ መጠን፣ በነማን ይዞታ ስር እንደነበሩ፤ የተሽከርካሪዎቹ ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ የመረጃ ቋዋት አለመኖሩን ፤

139. በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በተሽከርካሪ የግል ማህደር ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው መረጃዎች ማለትም ተሽከርካሪው የተገዛበት ዓመተ ምህረት፣ የተገዛበት ዋጋ ያልተቀመጠ መሆኑ ፣ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ በተሟላ

ሁኔታ አለመያዝ፣ ተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት፣ ቅባት፣ ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣ የተጓዛው ኪሎ ሜትር መጠን፣ በእነማን ይዞታ ስር እንደነበሩ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉት መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖር ፤

140. በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የሰሌዳ ቁጥር /4-14152፣ 4-14782፣ 4-18469/፣ 4-15386/ የሆኑት 4 ተሽከርካዎች ሊብሬ የሌላቸው መሆናቸውን ፤ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪውን የሕይወት ታሪክ የሚያሳይ ማህደር በተሟላ መልኩ አለመያዙን፣ ዩኒቨርስቲ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገላቸው 12 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው ፤ ዋጋቸው የማይታወቅ 4 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሊብሬ የሌላቸውና ባለቤታቸው የማይታወቅ ሁለት መኪኖች፣ እንዲሁም አንድ ተሽከርካሪ ከፍተኛ አደጋ ደርሶበት ለወራትና ለበርካታ አመታት ቆሞ መገኘቱ፤

141. በደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣ የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት፣ ቅባት ፍጆታ መጠን ፤ የጥገና ወጪ የተጓዘው ከሎ ሜትር መጠን በእነማን ይዞታ ስር እንደነበሩ፣ የተሽከርከሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖሩን ፤

142. በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣ተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ ፣ዘይት፣ ቅባት ፍጆታ መጠን የጥገና ወጪ የተጓዘው ኪሎ ሜትር መጠን በእነማን ይዞታ ስር እንደነበረ፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አካቶ የያዘ መረጃ አለመኖሩ፣ የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን መዝግቦ አለመያዙን ከመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ወጥ /standardized / እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ መኖሩን፣ ስለነዳጅ አጠቃቀም ስልጠና መሰጠቱን እና ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዘጋጀታቸውንና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፤

143. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

144. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ በግብርና ሚ/ር፣ በጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በማእድን ሚ/ር፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በባህር ዳር ስታትስቲክስ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ወጥ በሆነ መንገድ ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን እና በተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች ሙሉ በሙሉ በነዳጅ አጠቃቀም ቁጥጥር ላይ በቂ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን ተገኝቶ ነበር፡፡

145. የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለሁሉም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ እንደሚገባ፣ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና በመስጠት የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር ቢደረግ ነዳጅን በክህሎት ለመጠቀም እንደሚያስችል፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሽርካሪዎች በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ ሊያደርግ እንደሚገባ፣ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በዚሁ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራ ሊከናወን እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

146. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ሁሉም የመንስት መ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ 2005 ዓ.ም ና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ፣ የውስጥ አሰራር መዘርጋቱን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ እንዲሁም መ/ቤቶች ለአሽከርካሪዎች ሥልጠና መስጠታቸውን ክትትል እንደሚደረግ እና በ 2005 ዓ.ም እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን፣ በመ/ቤቶች ቅፆችን ተከትሎ መሠራቱን በማረጋገጥ ፣ የተላኩትን ቅፆች ስራ ላይ ማዋላቸውን የሚረጋገጥ መሆኑን እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

147. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

148. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣(ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ አዘጋጅቶ ያልሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

149. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ስልጠና ሰጥቶዋቸው እንደማያውቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

150. እንዲሁም በፍትህ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚሰራ በቂ ባለሞያ የሌለ መሆኑን፣ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ በክፍሉ በተሟላ ሁኔታ የተመደቡ ሠራተኞች አለመኖራቸውና ስልጠናም ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ በሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት ጽ/ቤት የጥገና አስተባባሪና የተሽከርካሪ ስምሪት ኦፊሰር የተሟላ አለመሆኑ እና የተሽከርካሪ ስምሪትና ቁጥጥር ስልጠና አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

151. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣በማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተሸርካሪዎች በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ እንደማያደርግ መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

152. በኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎች ተመዝግው አለመያዛቸውን፣ የ.ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ላይ የተገለጹት ቅጾች ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፤

153. በሰመራ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ አጠቃቀም ከቅጽ 01 እስከ ቅጽ 013 ያሉት በመመሪያው መሠረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለሥልጣን፣ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ በብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ጽ/ቤት፣ በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በመንግስት ኰሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን፣ በአገር አቀፍ ትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ፣ በደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ፣

የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ላይ በቅጥያ የተቀመጡትን ሰነዶች በተሟላ መልኩ አለመጠቀምና መረጃዎችን ተመዝግበው አለመያዙን፤

154. በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ በመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተሽከርካሪ ስምሪትና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መጠቀሚያ የሆኑትን ቅጽ 10 እና 12ን አለመጠቀሙን፣ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ላይ የተገለጹት ቅጾች ማለትም ቅጽ 02፣ 03፣ 04፣ 05፣ 07፣ 08፣ እና 13 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ፣ በአካባቢና ደን ሚኒስቴር በተሽከርካሪ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ቅጽ ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 13 ያሉት አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ ፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 32/2004 ውስጥ የሚገኙ የተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም ቅፆች ማለትም ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 13 ሥራ ላይ ያልዋሉ መሆናቸውን፤

155. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪው ሲሰማራ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ለሥራ የሄደበትና የሚመለስበት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የማይምዘገብ መሆኑን እንዲሁም የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 13 በሥራ ላይ ያልዋሉ መሆናቸውን፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ነዳጅ ሲቀዳ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ለሥራ የሄደበትና የሚመለስበት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የማይምዘገብ መሆኑ እንዲሁም የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 13 በሥራ ላይ ያልዋሉ መሆናቸው ፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም ቅፆች ማለትም ቅጽ 01፣05፣07፣09 በሥራ ላይ ያልዋሉ መሆናቸውን፤

156. በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ለነዳጅና ቅባት በኪሎ ሜትር የፈጀውን መጠን ለመቆጣጠርና ለክትትል የሚያገለግለውን መመሪያ ቀጥር 32/2004 ቅጽ 02 በአገልግሎት ላይ እንዲውል ያላደረገ መሆኑን፣ በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል የመ/ቤቱ የተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም ቅፆች ማለትም ቅጽ 02፣04፣07፣08 እና 12 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የተሽከርካሪ ስምሪትና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ

ከተገለጹት መካከል ለአገልግሎት መዋል የሚገባቸውን ቅጾች ቅጽ4 እና 13ትን አለመጠቀማቸውን፤

157. በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎችን የነዳጅና የቅባት በኪሎ ሜትር የፈጀውን ለመቆጣጠርና ለክትትል የሚያገለግለውን መመሪያ 32/2004 ቅጽ 02 በአገልግሎት ላይ ቢውልም ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል እንዲላክ አለመደረጉን፣ በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ በተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ላይ የተገለጹት ቅጾች ማለትም ቅጽ 01፣02፣05፣07፣10፣12፣13 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ፣ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም ቅፆች ቅጽ 01፣02፣ 04፣ 05 ፣01፣012 ያልተጠቀሙ መሆኑን፤

158. በመቱ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም ቅፆችን /ቅጽ 01 02 05 / አሟልቶ አለመጠቀማቸውን የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

159. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በ2006 በጀት አመት 948፣ በ2007 በጀት ዓመት 1890 እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት 1173 የሚሆኑ ከፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች፣ የውስጥ ኦዲተሮች እንዲሁም የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች አመራሮችና ባለሙያዎች በድምሩ 4011 ለሚሆኑ በቋሚ ንብረት አስተዳደር ማኑዋል፣ እስቶክ ማናጅመንት ማኑዋል እንዲሁም የተሸከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ላይ ከ3 እስከ 5 ቀን የሚደርስ ስልጠና በኤጀንሲው ባለፉት ሶስት አመታት መሰጠቱን ገልፀዋል፡፡

160. ይሁን እንጂ በቂ ማስረጃ ባይቀርብም በኤጀንሲው የተሰጠው ስልጠና ስለነዳጅ አጠቃቀም ሳይሆን ስለቋሚ ንብረት አስተዳደር ማኑዋል፣ ስለእስቶክ ማናጅመንት ማኑዋል እንዲሁም ስለተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን፣ ስለተሽከርካሪዎች ብዛት፣ ዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት እና ኦዲትን በተመለከተ፤

161. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

162. በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ አለመያዛቸው እና ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እስከ አሁን የተደረገ ኦዲት አለመኖሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

163. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በዚሁ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራ ሊከናወን እንደሚገባ፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ መያዙ መ/ቤቶች ያሏቸውን ተሽከርካሪዎች ለማወቅ እንደሚያስችል እና የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት በማከናወን የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ሊያጠናክር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

164. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መንኤ/ፈ-7/1/871/ በቀን 13/09/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል በፕሮግራም ተይዞ በመ/ቤቶች ኦዲትና ክትትትል የሚደረግ መሆኑን እና በ 2006 ዓ.ም ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

165. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

166. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ(ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር ፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር

ሥርዓት በመዘርጋት በዚሁ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራ አከናውኖ እንደማያውቅ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፣

167. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ የያዘ መሆኑን ከዓመታዊ የተሽከርካሪ መረጃ ለማወቅ መቻሉ፣

168. በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በማዕድ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር ፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት አከናውኖ እንደማያውቅ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

169. በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር በተመለከተ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት በሒደት ላይ ያለና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ስለተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት መጠናቱ፣

- በተወሰኑ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋቱ፣

- የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለተወሰኑ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ መስጠቱ፣

- የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሽርካሪዎች በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ ማድረጉ፣

- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ የያዘ መሆኑን፣

- የፌዴራል መንግሥት የተሸከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ወጥቶ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ

  መኖሩ ታውቋል፡፡

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና አብዛኛዎቹ የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት አለማካሄዳቸውን፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት የሌላቸው መሆኑን፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደበው በጀት በዓመቱ የታቀደውን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ በጥናት ላይ አለመመስረቱን፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ አለመጠቀማቸውን፣
- ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ አለመሆኑን፣
- ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ መሠረት ያደረገ አለመሆኑን፣

- በሁሉም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ አለመኖሩን እና በሥራ ላይ አለመዋሉን፣

- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የማይታወቅ እና ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑን፣

- የፌደራል መንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የኪ/ሜትር ቆጣሪ /ጌጅ/ የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ስራ ላይ መሰማራታቸው፣

- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ያልተዘረጋ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣

- እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት በነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ በወቅቱ እርምጃ አለመወሰዱን፣

- የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በቂ ስልጠና አለመሰጠቱን፣ የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር አለመደረጉን፣

- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት እና የክትትልና ግምገማ ሥራ አለመከናወኑን፣

- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት አለመከናወኑን፣

እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

170. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

171. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በክትትል ኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡